# መልካም አዲስ ዓመት !

የታሪክ አምድ ነባራዊ፣ ምድረ-ህይወት ፍልስፍና፣
መውጣት መውረድ፣ የዓለም ህግ፣ የተፈጥሮ ገጽ ሆነና፣
ጊዜ ክፉ፣ ጊዜ ደጉ. .፣ እጥፍ-ዘርጋ፣ ዘመም-ቀና. .፣
አንዴ ጽልመት. .፣ አንዴ ብርሃን. .፣ ባለታሪክ፣ ባለዝና፤
ስትወድቂ. .፣ ስትነሺ. . .፣ በዘመናት ጉዞሽ ሂደት፣
ለዚህ ደረስሽ፤ እልልልል! ሁለት ሺ ሰባት ዓመት!

ባለፊደል፣ ባለቀመር. . . .፣ የባህል ጌጥ መናኸሪያ፣
የእምነት አውራ፣ የእግዚአብሔር ቤት፣ የቃል-ኪዳኑ ማደሪያ፤
በመለኮት ብፁዕ ጸጋ፣ ዙሪያ-ገባ የተከበብሽ፣
በፈጣሪ ጥበቃ ስር፣  በኃያል ክንዱ የተደገፍሽ፤
‘አበቅቴ ውሉን ቢስት’፣ የዘመመ ቢመስል ቀኑ፣
እርኩስ መንፈስ ቢጣባሽም፣ ቢያስጨንቅሽ ሰቀቀኑ፣
ያምላክሽ ኃይል፣ ብርቱ ክንዱ፣ በልጆችሽ መንፈስ አድሮ፣
እማይቀር ነው ትንሣኤሽ፣ አዲስ ዘመን ዓመት ቆጥሮ፤
እስከዚያው ግን ይመስገነው፣ ትንፋሽሽም በመኖሩ፣
መልካም ዓመት! ለቅን ሕዝብሽ! ለውብ ገላሽ፣ ላገር-ምድሩ!

የነጻነት ቀንዲል ዓርማ፣ ለልጆችሽ ብርቱ አለኝታ፣
የታመቅሽው ገሞራ-እሳት፣ በልባቸው ደም ትርታ፣
ስትጠቂ እሚጮኹት፣  ደስ ሲልሽ  እሚደምቁት፣
በሄዱበት አንቺን ይዘው፣ እሚያመልኩሽ እንደ ጽላት፣
እንደ ጨው ዘር ተበትነው፣ ባለም ዙሪያ ሰፍረው ላሉ፣
ይድረሳቸው ለውዶችሽ፣ ያዲስ ዓመት ተስፋ ቃሉ!

አንቺን ብለው እየማሉ፣ ለህልውናሽ ያደሩ፣
የትውልዱ ባላደራ፣ ስም ዝናሽን ያስከበሩ፤
ቤታቸውን ክፍቱን ጥለው፣ ለብዙኃን ሲታገሉ፣
ባረመኔ፣ በግፈኞች - ከወህኒ-ቤት፣ “ባዶ ሰድስት” የተጣሉ፣
ለሕዝብ ድምፅ፣ ለጀግኖችሽ፣ ለአጋሮችሽ የቁርጥ ቀን፣
ጭለማው ያከትም-ዘንድ፣ በአዲስ ዓመት ተስፋ ብርሃን!

የግፍ ጽዋው ሞልቶ ሲፈስ፣ ውርደትሽን ያልታገሱ፣
በራሳቸው ልዩ ቋንቋ - ሊታደጉሽ የተነሱ፣
ዋሻ፣ ፈፋ፣ ሽንተረሩ. .፣ ዱሩ ቤቴ ብለው ከተው፣
አጋም-ቀጋ፣ ሾላ. .በልተው፣ በእፍኝ ከውሃሽ ተጎንጭተው፣
ለመስዋዕት ለቆረጡ፣ ባንቺው ፍቅር ለነደዱ፣
መልካም ብሩህ አዲስ ዓመት! ጨርቅ ይሁንላቸው መንገዱ!

እንደ የዋኋ ላሜ ቦራ፣ በሾንጉርጉር የናት ሆድሽ፣
እሳት ወልደሽ፣ እንዳትልሽው ለሚፈጅሽ፣
እንዳትተይው፣ እሱም ልጅሽ. . .፣
ልቦናውን አምላክ ቸሮት፣ ከእኩይ-መንፈስ ተላቆ፣
ከበደለሽ ውድ እናቱ፣ ከእህት -ወንድሞቹ ታርቆ፣
ትሆን ዘንዳ፣ ምስኪን ጎጆሽ፣ ሰላም፣ ደስታ. .የሞላባት፣
ህሊናውን መፈተሻ፣ ይሁንለት አዲስ ዓመት!

ህመምሽ አሳስቧቸው፣ ለፈውስሽ ለሚቀምሙ፣
ቅጠል በልተው. .በምህላ. .፣ በዱአ. .ለታደሙ፣
ለሰላምሽ በሰላም መንገድ፣ እምቢኝ ብለው ለሚታገሉ፣
ፍትህ-አልባ ጉልበተኞችን፣ ከእንግዲህስ በቃ ላሉ፣
ባዲስ ዓመት፣ ባዲስ ብራ — ይስመር ትግሉ ደምቆ ያብራ!

የፍቅር እምነት ማተብ ገጽሽ፣ ህብረ-ቀለም ውብ ሰንደቅሽ፣
የክብር አልባስ፣ የክት ልብስሽ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይሽ፣
ትውለብለብ ለዘላለም፣ ከፍ ብላ፣ በአየር-ምድርሽ!

ከምዕራብ እስከ ምስራቅ፣ ከደቡብ . .እሰሜን ጫፍ፣
የጥቁር አፈርሽ ግኝቶች፣ የሰፈሩ ባንቺው ማዕቀፍ፣
የክርስቶስ፣ የአላህ ልጆች. . .፣ ፍጥረተ-ዓለም ያንቺ የሆኑ፣
ብሩህ ተስፋ፣ የህይወት ምንጭ፣ ይሁንላቸው ዘመኑ!

የዜጎችሽ ክብር ኩራት፣ ረቂቅ ውበት መጎናጸፊያ፣
መልካም አዲስ ዓመት ይሁንልሽ! እናት ሀገር ኢትዮጵያ!

ጌታቸው አበራ
ጳጉሜን 5 ቀን 2006 ዓ/ም
(ሰፕቴምበር 2014)

፪ሺ፯ ዓ/ም
2007